Library
Copy

በኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

# በድርቁ ሳቢያ የደረሱ ዲሞግራፊያዊ ለውጦች ጥናት - 1980 ዓ.ም

## የመረጃ ሰብሳቢዎች መመሪያ

አዲስ አበባ
የካቲት 1980 ዓ.ም

316.3
ETH
MAN

19/4/88


ገጽ

ዓምድ 26— ከአሁኑ የቤተሰብ ኃላፊ ጋር የነበራቸው ዝምድና ........................ 11

ዓምድ 27— የቀድሞ አባላት ጾታ ................ 11

ዓምድ 28— ድርቁ ሲጀምር ቤል የቀድሞ አባላት የነበራቸው ዕድሜ ........................ 11

ዓምድ 29— የቀድሞ አባል የነበሩት በድርቁ ምክንያት ሙተዋል? ...................... 12

ዓምድ 30— ከቤተሰቦችዎ አባላት መሐከል የኮበለለ አባል ይገኛል? /ካለ ብዛቱን ጥቀስ/ ....... 12

ዓምድ 31— ወደ ሠፈራው ከመምጣትዎ በፊት የነበረው ቤተሰብ በምን ሁኔታ ላይ ይገኛል? .... 13

ዓምድ 32— በኣርቦ ገምት ለ ኑሮ /ኣርሻ፣ጤና፣አየር፣... ወዘተ/ ሠፈራው ይሻላል ወይስ የድሮው ሥፍራ .......................... 13

ዓምድ 33— ለወደፊቱ በሠፈራ መቆየት ይመርጣሉ ወይስ መመለስ? 13

ዓምድ 34— ወደ ቀድሞ ሥፍራ መመለስ የሚፈልጉ ከሆነ ምክንያቱ ምንድነው? ...................... 14

ቀን ቀን የሚታወሱ ታሪካዊ ድርጊቶች የተፈጸሙበት ዘመን ......... 15

የትግራይና የወሎ ክፍለሀገራት አውራጃ፣ ወረዳና ከተማ ዝርዝር .... 17

## በድርቅ ሳቢያ የደረሱ ዲሞግራፊያዊ ለውጦች ጥናት

ይህ ጥናት በከፋ፣ በኢሉባቦር፣ በወለጋ፣ በጎጃምና በጎንደር የሠፈራ አካባቢዎች በሰግሰጋ ሠፍረው ከሚገኙ ቤተሰቦች ውስጥ በናሙና በተመረጡ ቤተሰቦች መሐከል በድርቅ ወቅት ምን ያህል ሰው እንደሞተባቸውና ስለ ሠፈራው ያላቸውን አስተያየት እንዲያመለክት የታቀደ ነው:: በዚህ ጥናት የሚሰበሰቡት መረጃዎች የመልስ ሰጭዎችን ከፍተኛ ትብብር የሚጠይቁ ናቸው:: ምክንያቱም መጠይቁ ከዚህ በፊት ሠፋሪዎች የደረሰባቸውን የዘመዶቻቸውን በሞት መለየት የሚያስታውሳቸው በመሆኑና በተጨማሪም ስለ ሠፈራው ያላቸውን አስተሳሰብ የሚያመለክት በመሆኑ ነው:: ስለዚህ ትክክለኛውን መረጃ ለማግኘት ከፍ ያለ የመግባባት መንፈስ በመልስ ሰጭዎች ለማሳደር ጥረት መደረግ ይኖርበታል:: በጥናቱ የሚሰበሰቡ መረጃዎች፣ ለጠቅላላው የቤተሰብ አባላት ስም፣ ዝምድና፣ ጾታና ብሔረሰብ ሲሆኑ ዕድሜአቸው አሥር ዓመትና በላይ ለሆናቸው ደግሞ የጋብቻ ሁኔታ፣ የጋብቻ ታሪክ፣ ከየት መጥተው እንደሰፈሩ በድርቅ ምክንያት ያጧቸውን የቤተሰቦቻቸውን አባላት ብዛት እና የሥራ ሁኔታ ሲሆን ከቤተሰብ ኃላፊዎች ደግሞ ከሠፈራ የኮበለሉ አባላት ካሉ ብዛታቸውን፣ የቀድሞው ቤተሰባቸው በምን ሁኔታ እንደሚገኝ፣ ሠፈራውን ከድሮው ሥፍራቸው ጋር በማስተያየት የትኛው እንደሚሻል ያላቸውን አስተሳሰብና ለወደፊቱ በሠፈራው ለመቆየት ያላቸው አስተያየት ናቸው:: በተጨማሪም የቤተሰብ ኃላፊዎች ድርቁ ሲጀምር ይኖሩበት የነበረው ቤተሰብ አባላት የነበሩት በዝርዝር ጾታና ዕድሜአቸው እየተለየ ተመዝግበው በድርቅ ምክንያት ሞተው እንደሆነ ይጠየቅላቸዋል::

## በድርቅ ባቢያ የደረሱ ዲሞግራፊያዊ ለውጦችና የሠፋሪያዎች

## አስተባሰብ ጥናት መጠይቅ አሞላል መመሪያ

ዓምድ 1 — ክፍለ ሀገር

ጥናቱ የሚካሄድበት ክፍለ ሀገር ስም በተሰጠው ክፍት ቦታ ይመዘገባል።

ዓምድ 2 — አውራጃ

ጥናቱ የሚካሄድበት አውራጃ ስም በተሰጠው ክፍት ቦታ ይመዘገባል።

ዓምድ 3 — ወረዳ

ጥናቱ የሚካሄድበት ወረዳ ስም በተሰጠው ክፍት ቦታ ይመዘገባል።

ዓምድ 4 — መደበኛ/ሰግሰጋ

ጥናቱ የሚካሄደው በሠፈራ አካባቢ ከሆነ ኮድ 1 ሲመዘገብ ሰግሰጋ በተካሄደባቸው ገበሬ ማሕበራት የሚካሄድ ከሆነ ደግሞ ኮድ 2 ይመዘገባል።

ኮድ 1 — መደበኛ
ኮድ 2 — ሰግሰጋ

ዓምድ 5 — ሠፈራ አካባቢ/ገበሬ ማሕበር

ጥናቱ የሚካሄደው በሠፈራ አካባቢ ከሆነ የሠፈራ አካባቢው ስም ይመዘገባል። ጥናቱ የሚካሄደው በገበሬ ማሕበር ውስጥ ከሆነ ደግሞ የገበሬ ማሕበሩ ስም ይመዘገባል።

ዓምድ 6 — የምርጫ ተራ ቁጥር

ቤተሰቡ የተመረጠበት የምርጫ ተራ ቁጥር በካርድ ዓምድ 14—15 ላይ ይመዘገባል።

ዓምድ 7 — የቤተሰብ ተከታታይ ተራ ቁጥር

የቤተሰብ ተራ ቁጥር ከሕዝብ ቆጠራው መጠይቅ /ዓምድ 13/ ወደዚህ ዓምድ ይወራረሳል።

ዓምድ 8 — ተራ ቁጥር

የቤተሰቡ አባላት ተራ ቁጥር ከ01 እስከ 10 ድረስ ተመዝግቧል። የቤተሰቡ አባላት ከአሥር በላይ ከሆኑ ደግሞ የሚከተለውን ገጽ በመጠቀም 01 የነበረውን ወደ 11፣ 02 የነበረውን ወደ 12 በመለወጥ መጠይቁ ይሞላል። የቤተሰቡ አባላት ከአሥር በላይ በሚሆኑበት ወቅት በመጀመሪያው ገጽ ግርጌ ላይ "ይቀጥላል" የሚል ጽሑፍ በጉልህ የሚጻፍ ሲሆን በሁለተኛው ገጽ ጫፍ ላይ ደግሞ "የቀጠለ" የሚል ቃል መጻፍ ይኖርበታል።

ዓምድ 9 — የቤተሰብ መደበኛ አባላት ሙሉ ስም

የቤተሰቡ መደበኛ አባላት በጠቅላላ በዚህ ዓምድ ላይ ተዘርዝረው ይመዘገባሉ። የቤተሰብ አባላት የሚባሉ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ አብረው የሚኖሩና ምግባቸውን በአንድነት አብስለው የሚመገቡ ግለሰቦች ናቸው። አብዛኞቹ የቤተሰብ አባላት በሥጋ ወይም በጋብቻ የሚዛመዱ ሲሆኑ ከቤተሰቡ ጋር በአንድነት የሚኖሩና ምግባቸውን የሚካፈሉ ሌሎች ግለሰቦች ካሉ፣ እነዚህም እንደ ቤተሰብ አባል ይቆጠራሉ። የአንድ ቤተሰብ አባላት በአንድ ቤት ውስጥ ወይም በተቀራረቡ ቤቶች ውስጥ ሊኖሩ ይችላሉ። እንደዚሁም በአንድ ቤት ውስጥ በአብዛኛው አንድ ቤተሰብ ሲኖር አንዳንድ ጊዜ ከአንድ በላይ የሆኑ ቤተሰቦች በደባልነት ሊኖሩ ይችላሉ። ደባል የሆኑ ቤተሰቦች በሚያጋጥሙበት ወቅት የተመረጠው ቤተሰብ አባላት ብቻ ይመዘገባሉ።

መደበኛ የቤተሰብ አባላት የሚባሉት በምዝገባው ወቅት ከቤተሰቡ ጋር የሚገኙ አባላትና በተለያዩ ምክንያቶች /ለምሳሌ ዘመድ ለመጠየቅ፣ ለሕክምና፣ ለገበያ፣ ወዘተ./ ለጥቂት ጊዜ ከቤተሰቡ የተለዩትን ያጠቃልላል። የቤተሰብ አባል የነበሩና ከቤተሰቡ ከተለዩ ከስድስት

ወራት በላይ የሆናቸው ግለሰቦች ግን ስቤተሰቡ አባልነት አይመዘገቡም፡፡ በዚሁም አንጻር በእንግድነት ወደ ቤተሰቡ የመጡ ግለሰቦች በቤተሰብ አባልነት አይመዘገቡም፡፡ ነገር ግን ወደ ቤተሰቡ የመጡት በቋሚነት ለመቆየት ወይም ከስድስት ወር በላይ ለመቆየት ከሆነ እንደ ቤተሰብ አባል ይቆጠራሉ፡፡

ከአንድ በላይ ሚስቶች ያሉት ቤተሰብ በሚያጋጥምበት ወቅት ባልየውና ሚስቶቹ ከልጆቻቸው ጋር በአንድ ቤት ውስጥ እየኖሩ ምግባቸውን በአንድነት አብስለው የሚመገቡ ከሆኑ እንደ አንድ ቤተሰብ ይቆጠራሉ፡፡ ነገር ግን ሚስቶቹ ምግባቸውን ለየብቻቸው አብስለው የሚመገቡ በሚሆንበት ወቅት እንደተለያዩ ቤተሰቦች ይቆጠራሉ፡፡ በዚህን ወቅት ባልየው አብዛኛውን ወቅት ከሚያሳልፍበት ቤት ውስጥ እንደ አባል ይቆጠራል፡፡

የቤተሰቡ አባላት በሚመዘገቡበት ወቅት የቤተሰብ ኃላፊው በመጀመሪያው መስመር መመዝገብ ይኖርበታል፡፡ ስለዚህ ለኃላፊው የሚሰጠው ኮድ '1' በተራ ቁጥር 01 ትይዩ ተመዝግቦ ይገኛል፡፡ የቤተሰብ ኃላፊ የሚባለው ከቤተሰቡ አባላት መሃከል ቤተሰቡን ይመራል፣ ወይም ያስተዳድራል ተብሎ የሚታመንበት አባል ነው፡፡ የቤተሰቡ አባላት አመዘጋገብ ቅደም ተከተል ሁልግዜ በተመሳሳይ መልክ የሚከናወን ሲሆን አባላት ባይመዘገቡ እንዳይዘነጉ ይረዳል፡፡ የአመዘጋገቡ ቅደም ተከተልም በሚከተለው መልክ ሊሆን ይችላል፡፡

1 — ኃላፊ

2 — የኃላፊው /የኃላፊዋ/ ባለቤት

3 — ወላጆች

4 — ያገቡ ልጆች

5 — ያላገቡ ልጆች/በዕድሜ ቅደም ተከተል

6 — ሌሎች ዘመዶች

7 — የቤት ውስጥ ሠራተኞችና ሌሎች ዝምድና የሌላቸው

ዓምድ 10 — ዝምድና

የቤተሰቡ አባላት በጠቅላላ ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያላቸው ዝምድና ተጠይቆ በዚህ ዓምድ ውስጥ በተሰጡት ኮዶች አማካይነት ይመዘገባል።

ኮድ 1 — ኃላፊ /መጠይቁ ላይ የተሞላ/

ኮድ 2 — ባል/ሚስት

ኮድ 3 — ልጅ

የኃላፊው ወይም የኃላፊው ባለቤት ወይም የሁለቱ ልጆች ወይም የማደጎ ልጆች

ኮድ 4 — ወንድም/እህት

የኃላፊው ወይም የኃላፊው ባለቤት ወንድም ወይም እህት

ኮድ 5 — አባት/እናት

የኃላፊው ወይም የኃላፊው ባለቤት አባት ወይም እናት

ኮድ 6 — ሌላ ዘመድ

ኮድ 7 — ዘመድ ያልሆኑ

ዓምድ 11 — ጾታ

የቤተሰቡን አባላት ጾታ በመጠየቅ ከታች በተዘረዘሩት ኮዶች አማካይነት መልሱ ይመዘገባል።

ኮድ 1 — ወንድ

ኮድ 2 — ሴት

ዓምድ 12 — ዕድሜ

የቤተሰቡ አባላት ከተወለዱ ጀምሮ ጥናቱ እስከ ተካሄደበት ቀን ድረስ ስንት ዓመት እንደኖሩ ተጠይቆ መልሱ በኮድ ዓምድ 22 — 23 ይመዘገባል። ዕድሜ የሚመዘገበው በጨረሱት ሙሉ ዓመት ወይም ባከበሩት የልደት ቀን ብዛት መሆን አለበት። ለምሳሌ አርባ ዓመት ከአንድ ወር የሆነው ወይም አርባ ዓመት ከአሥራ አንድ ወር የሆነው አባል የሚመዘገብለት ዕድሜ 40 ብቻ መሆን አለበት። ዕድሜ የሚመዘገበው በሁለት አሃዞች ሲሆን ዕድሜአቸው 97 ዓመትና በላይ ለሆናቸው የቤተሰብ ኃላፊዎች "97" ይመዘገብላቸዋል።

የቤተሰቡን አባላት ዕድሜ በትክክል ማግኘት ለጥናቱ ትልቅ ጠቀሜታ ስለሚኖረው ምንም እንኳ አንዳንድ ዕድሜአቸውን በትክክል የማያውቁ አባላት ቢያጋጥሙ የተለያዩ የዕድሜ ማግኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ትክክለኛውን ዕድሜ ማግኘት ያስፈልጋል:: ትክክለኛ ዕድሜን ለማግኛ አንዱ ዘዴ ዕድሜአቸውን በትክክል ከሚያውቁ የቤተሰቡ አባላት ዕድሜ በመነሳት የሌሎቹን መገመት ይሆናል:: ለምሳሌ ኃላፊው ልጃቸውን በወለዱ ጊዜ የነበራቸው ዕድሜ ከታወቀና በተጨማሪም የመጀመሪያ ልጃቸው ዕድሜ ከታወቀ አሁን ያላቸውን ዕድሜ ማስላት ይቻላል:: በተጨማሪ ጋብቻ በፈጸሙበት ጊዜ የነበራቸው ዕድሜ እና ምን ያህል ዓመት በጋብቻ እንዳሳለፉ ከታወቀ አሁን ያላቸውን ዕድሜ መወቅ ይቻላል:: በተጨማሪም ዕድሜአቸውን ከአንዳንድ ያለፉና የሚታወሱ ድርጊቶች ጋር በማነጻጸር መናገር ይችሉ ይሆናል:: እነዚህ ድርጊቶች ከተፈጸሙ ስንት ዓመት እንዳለፉ ማወቅ የአባሉን ዕድሜ ለማወቅ ይረዳል:: በዚህ መመሪያ መጨረሻ ገጾች ላይም ለዚህ እንዲያገለግል አንዳንድ ታሪካዊ ድርጊቶች የተፈጸሙበትን ወቅት የሚገልጽ መረጃ ተዘርዝሮ ቀርቧል:: ብዙ ግለሰቦች ዕድሜአቸውን በዜሮ ወይም በአምስት በሚያልቁ አሃዞች መናገር ስለሚቀናቸው ወይም ስለሚወዱ እንደዚህ ያለ ሁኔታ ሲያጋጥም ትክክለኛ ዕድሜአቸውን ለማወቅ ተገቢውን ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል::

<u>ዓምድ 13 — ብሄረሰብ</u>

እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ብሄረሰቡ ተጠይቆ በዓምዱ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል:: የብሄረሰቡ ኮድ የሚሞላው በዋናው መሥሪያ ቤት ስለሆነ ካርድ ዓምድ 22 — 23 ባዶ መተው ይኖርባቸዋል:: ከሁለት ከተለያዩ ብሄረሰቦች ለሚወለዱ ግለሰቦች፣ ግለሰቦቹ ወይም ወላጆቻቸው በሚገልጹት መሠረት የአንደኛው ብሄረሰብ ስም ይመዘገብላቸዋል::

<u>ዓምድ 14 — የጋብቻ ሁኔታ</u>

ዕድሜአቸው አሥርና ከአሥር ዓመት በላይ የሆናቸው የቤተሰብ አባላት የጋብቻ ሁኔታቸው ተጠይቆ ከታች በተሰጡት ኮዶች አማካይነት በካርድ ዓምድ 26 ትክክለኛው ኮድ ይመዘገባል:: ጋብቻ ተብሎ የሚወሰደው በሕጋዊም ሆነ በባህላዊ መንገድ አንድ ወንድና አንድ ሴት ባልና ሚስት ሆነው አንድ ላይ የሚኖሩበት ሁኔታ ሁሉ ነው::

የጋብቻውን ሁኔታ ለማመልከት ከዚህ በታች የተመለከቱት የጋብቻ ዓይነቶችና ኮዶቻቸው ተሰጥተዋል፡፡

ኮድ 1 — ፈጽሞ ያላገቡ

ኮድ 2 — በትዳር የሚገኙ

ኮድ 3 — የሞተባቸው

ባሎቻቸው ወይም ሚስቶቻቸው የሞተባቸውና ከዚያ ወዲህ ያላገቡ

ኮድ 4 — የተፋቱ

ከባሎቻቸው ወይም ከሚስቶቻቸው ጋር የተፋቱና ከዚያ ወዲህ ያላገቡ

ዓምድ 15 — የጋብቻ ታሪክ

ዕድሜአቸው አሥር ዓመትና ከዚያ በላይ የሆናቸው አባላት ወደ ሠፈራው ከመጡ ወዲህ ስንት ጊዜ እንዳገቡ ተጠይቀው መልሱ በሚከተሉት ኮዶች አማካይነት ይመዘገባል፡፡

ኮድ 1 — ፈጽሞ ያላገቡ

ኮድ 2 — ከሠፈራ በፊት ካገቡአቸው ባለቤታቸው ጋር የሚገኙ

ኮድ 3 — ሠፈራ ከመጡ ወዲህ አንዴ ያገቡ

ኮድ 4 — ሠፈራ ከመጡ ወዲህ ሁለቴ ያገቡ

ኮድ 5 — ሠፈራ ከመጡ ወዲህ ሦስቴ ያገቡ

ኮድ 6 — ሠፈራ ከመጡ ወዲህ አራቴ ያገቡ

ኮድ 7 — ሠፈራ ከመጡ ወዲህ ከአራት ጊዜ በላይ ያገቡ

ዓምድ 16 — 17 — ወደ ሠፈራው ከመምጣትዎ በፊት የት ይኖሩ ነበር?

ዕድሜአቸው አሥር ዓመትና ከዚያ በላይ የሆናቸው የቤተሰብ አባላት ወደ ሠፈራ አካባቢው ከመምጣታቸው በፊት ይኖሩበት የነበረው ሥፍራ የሚገኝበት ክፍለ ሀገርና አውራጃ ስም በተሰጡት ክፍት በታዎች ይመዘገባል፡፡

የመጡበትን አካባቢ የሚገኝበትን አውራጃና ክፍለ ሀገር ስም የማያውቁ ግለሰቦች ካጋጠሙ ለማወቅ ይረዳ ዘንድ የወሎንና የትግራይን ክፍለ ሀገራት አውራጃ እና ወረዳ የሚያመለክት መረጃ ከዚህ መመሪያ ጋር ተያይዞ ቀርቧል፡፡

ዓምድ 18 — የቀድሞው ሥራያ ዓይነት ምን ነበር?

አሥር ዓመትና በላይ የሆናቸው የቤተሰብ አባላት ወደ ሠፈራው ከመምጣታቸው በፊት ሥራ እንደነበራቸው ወይም እንዳልነበራቸው ተጠይቀው ሥራ የነበራቸው በጠቅላላ አብዛኛውን ጊዜ ሥራቸው ምን ማድረግ እንደነበረ ተጠይቀው መልሱ በሚከተሉት ኮዶች አማካይነት ይመዘገባል።

ኮድ 01 — ሥራ ያልነበራቸው
ኮድ 02 — ገበሬ፣ ከብት አርቢ
ኮድ 03 — ቅጥር ገበሬ፣ ኣረኛ
ኮድ 04 — ጠላ፣ አረቄ ቸርቻሪ
ኮድ 05 — ነጋዴ /ጠጠላና አረቄ ነግድ ሌላ/
ኮድ 06 — ሸማኔ፣ ፈታይ
ኮድ 07 — ሸክላ ሠሪ
ኮድ 08 — ቀጥቃጭ
ኮድ 09 — የበሬዶ፣ የቅርጫት ወይም የሌሎች ምርቶች አምራች
ኮድ 10 — የጉልበት ወይም የሌሎች አገልግሎቶች ሥራ ሠራተኛ
ኮድ 11 — ሌሎች

ዓምድ 19 — የአሁኑ ሥራያ ዓይነት ምንድነው?

አሥር ዓመትና በላይ የሆናቸው አባላት በአሁኑ ጊዜ ሥራ እንዳላቸው ወይም ሥራ እንደሌላቸው ተጠይቀው፣ ሥራ ያላቸው ሁሉ ሥራቸው ምን ማድረግ እንደሆነ ተጠይቀው መልሱ ከላይ በተጠቀሱት ኮዶች አማካይነት ይመዘገባል።

ዓምድ 20 — የቀድሞው ሥራያን ከአሁኑ ጋር ሲያስተያዩት የትኛውን ይመርጣሉ?

ወደ ሠፈራው ከመጡ በኋላ የያዙትን ሥራ ቀድሞ ይሠሩት ከነበረው ጋር በማስተያየት የትኛውን የተሻለ ነው ብለው እንደሚመርጡ አስተያየታቸውን ተጠይቀው መልሱ በሚከተሉት ኮዶች አማካይነት ይመዘገባል።

ኮድ 1 — አይመለከትም

በአሁኑ ጊዜ ወይም በፊተኛው ወቅት ሥራ ስላልነበራቸው ለማስተያየት አይቻልም።

ኮድ 2 — የቀድሞውን
ኮድ 3 — የአሁኑን
ኮድ 4 — ልዩነት የለውም

የቤተሰቡ አባላት አመዘጋገብ በዓምድ 9 ላይ በተገለጸው መሠረት ሲሆን የተመረጠው ቤተሰብ ኃላፊ በዓምድ 9 ላይ በመጀመሪያው መስመር ላይ እንደተመዘገበ ሁሉ በዚህም ዓምድ ላይ በመጀመሪያው መስመር ላይ መመዝገብ ይኖርበታል።

ዓምድ 26 — ከአሁኑ የቤተሰብ ኃላፊ ጋር የነበራቸው ዝምድና

በዓምድ 25 ላይ ተዘርዝረው የቀረቡ ግለሰቦች ሁሉ ከአሁኑ የቤተሰብ ኃላፊ ጋር የነበራቸው ዝምድና ምን እንደነበረ በመጠየቅ መልሱ በሚከተሉት ኮዶች አማካይነት ይመዘገባል፤

ኮድ 1 — የአሁኑ ኃላፊ /መጠይቁ ላይ የተሞላ/
ኮድ 2 — ባል /ሚስት
ኮድ 3 — ልጅ
ኮድ 4 — ወንድም /እህት
ኮድ 5 — አባት /እናት
ኮድ 6 — ሌላ ዘመድ
ኮድ 7 — ዘመድ ያልሆኑ

ዓምድ 27 — የቀድሞ አባላት ጾታ

በዓምድ 25 ላይ ስማቸው የተዘረዘረው የቀድሞው ቤተሰብ አባላት ጾታ ተጠይቆ መልሱ በሚከተሉት ኮዶች አማካይነት ይመዘገባል፤

ኮድ 1 — ወንድ
ኮድ 2 — ሴት

ዓምድ 28 — ድርቁ ሲጀምር ሲላ የቀድሞ አባላት የነበራቸው ዕድሜ

በዓምድ 25 ላይ የተዘረዘሩት የቀድሞ አባላት ድርቁ ሲጀምር ሲላ የነበራቸው ዕድሜ ተጠይቆ መልሱ በዚህ ዓምድ ላይ ይመዘገባል። ዕድሜ የሚሞላው በሙሉ ዓመት ሲሆን ለዓምድ 12 በተሰጠው ማብራሪያ መሠረት ይሆናል። በዚህም መሠረት 97 ዓመትና ከዚያ በላይ የነበራቸው ግለሰቦች ሁሉ 97 ይመዘገብላቸዋል ማለት ነው።

ይህ ዓምድ በሚሞላበት ወቅት መታወስ የሚገባው ነገር ዕድሜ የሚመዘገበው የአሁኑ ወቅት ባይሆን ድርቁ ሲጀምር ሲል የነበረው መሆኑ ነው።

ዓምድ 29 — የቀደሞ አባል የነበሩት በድርቅ ምክንያት ሙተዋል?

በዓምድ 25 ላይ ስማቸው የተገለጸው ግለሰብ በድርቅ ምክንያት ሞተው ከነበረ ተጠይቆ መልሱ በሚከተሉት ኮዶች አማካይነት ይመዝገባል።

ኮድ 1 — አዎን

በድርቅ ምክንያት ለሞቱ

ኮድ 2 — የለም

በድርቅ ምክንያት ያልሞቱ

የአሁኑ የቤተሰብ ኃላፊ ስም በዓምድ 25 ላይ በመጀመሪያው መስመር ላይ ስለሚሞላ ዓምድ 29 ለዚህ ግለሰብ በመጠይቁ ላይ ተሞልቶ ይገኛል።

ዓምድ 30 — ከቤተሰቦችዎ አባላት መሐከል የኮበለለ አባል ይገኛል? /ካለ ብዛቱን ጥቀስ/

በተመረጠው ቤተሰብ ውስጥ በአባልነት ይኖሩ ከነበሩት ግለሰቦች መሐከል ከሠፈራው ውጪ ወደ ሌላ ሥፍራ ጠፍተው የሄዱ አባላት እንዳሉ የቤተሰብ ኃላፊው ተጠይቆ መልሱ በሚከተሉት ኮዶች አማካይነት ይመዝገባል።

ኮድ 0 — የለም

የቤተሰቡ አባላት ከነበሩት መሐከል ማንም የኮበለለ አይገኝም።

ኮድ 1 — አንድ

ኮድ 2 — ሁለት

ኮድ 3 — ሦስት

ኮድ 4 — አራት

ኮድ 5 — አምስት

ኮድ 6 — ስድስት

ኮድ 7 — ሰባት

ኮድ 8 — ስምንትና ከዚያ በላይ

ዓምድ 31 — ወደ ሠፈራው ከመምጣትዎ በፊት የነበረው ቤተሰብ በምን ሁኔታ ላይ ይገኛል?

የቤተሰብ ኃላፊው ቀድሞ ይኖርበት የነበረውን ቤተሰብ ከአሁኑ ጋር በማስተያየት፣ ቤተሰቡ አብሮ ወደ ሠፈራው መጥቶ እንደሆነ ወይም ተለያይቶ የሚገኝ እንደሆነ በሚከተሉት ኮዶች አማካይነት መልሱ ይመዘገባል።

ኮድ 1 — ቤተሰቡ በጠቅላላ ወደ ሠፈራው መጥቶ አሁንም አንድ ላይ ይገኛል
ኮድ 2 — ቤተሰቡ በጠቅላላ ወደ ሠፈራው መጥቶ በተለያዩ ቦታዎች ይገኛል
ኮድ 3 — ቤተሰቡ በአብዛኛው ወደ ሠፈራው መጥቶ አሁንም አንድ ላይ ይገኛል
ኮድ 4 — ቤተሰቡ በአብዛኛው ወደ ሠፈራው መጥቶ በተለያዩ ቦታዎች ይገኛል
ኮድ 5 — ቤተሰቡ በጥቂቱ ወደ ሠፈራው መጥቶ አንድ ላይ ይገኛል
ኮድ 6 — ቤተሰቡ በጥቂቱ ወደ ሠፈራው መጥቶ በተለያዩ ቦታዎች ይገኛል

ዓምድ 32 — በእርሶ ግምት ለኑሮ ለእርሻ፣ ጤና፣ አየር፣ ወዘተ/ ሠፈራው ይሻላል ወይስ የድሮው ሥፍራ?

የቤተሰቡ ኃላፊ በአጠቃላይ ለኑሮ፣ አሁን ሰፍረው የሚገኙበትን ቦታ ቀድሞ ይኖሩበት የነበረበትን ቦታ በማወዳደር የትኛው አካባቢ እንደ ሚሻል በሚገልጹት መሠረት መልሱ በሚከተሉት ኮዶች አማካይነት ይመዘገባል።

ኮድ 1 — ሠፈራ አካባቢ
ኮድ 2 — የድሮው ሥፍራ
ኮድ 3 — ልዩነት የለውም

ዓምድ 33 — ለወደፊቱ በሠፈራ መቆየት ይመርጣሉ ወይስ መመለስ?

ለዚህ ጥያቄ የቤተሰብ ኃላፊው የሚሰጡት መልስ በሚከተሉት ኮዶች አማካይነት ይመዘገብላቸዋል።

ኮድ 1 — ሠፈራው መቆየት
ኮድ 2 — መመለስ
ኮድ 3 — አልወሰኑም

ዓምድ 34 — ወደ ቀድሞ ስፍራ መመለስ የሚፈልጉ ከሆነ ምክንያቱ ምንድነው?

በዓምድ 25 ለወደፊት ወደ ቀድሞው ስፍራችን መመለስ እንመርጣለን በማለት ኮድ "2" የተመለሱቸው የቤተሰብ አባላት በጠቅላላ በዚህ ዓምድ ወደ ቀድሞው ሥፍራ ለመመለስ የፈለጉበት ምክንያት ይጠየቋቸዋል፡፡

ለዚህ ጥያቄ የሚሰጡት መልስ በሚከተሉት ኮዶች አማካይነት ይመዘገባል፡፡

ኮድ 1 — ከቤተሰብ ላለመለየት
ኮድ 2 — ከትውልድ ሥፍራ ላለመራቅ
ኮድ 3 — የአየር አለመስማማት
ኮድ 4 — የምግብ አለመስማማት
ኮድ 5 — የቀድሞውን ንብረት ላለመተው
ኮድ 6 — ድርቁ ስለተሻለው
ኮድ 7 — ሌላ

## ዋና ዋና የሚታወሱ ታሪካዊ ድርጊቶች የተፈጸሙበት ዘመን

| ተራ ቁጥር | ታሪካዊ ድርጊቶች | ድርጊቱ የተፈጸመበት ዓ.ም | እስከ 1980ዓ.ም ያለፉ ዓመታት |
|---|---|---|---|
| 1 | አጼ ምኒሊክ የነገሡበት | 1882 | 98 |
| 2 | ዘዋይ የተወረረበት /ከጅቡቲ እስከ አዲስ አበባ ያለው የባቡር መስመር የተዘረጋበት/ | 1886 | 94 |
| 3 | ራስ መንገሻና ራስ አሉላ ከኢጣሊያን ሠራዊት ጋር በኩዓቲት ላይ ጦርነት የገጠሙበት | 1887 | 93 |
| 4 | ራስ መንገሻ በኩዓቲትና በሰንአፌ ላይ በኢጣልያን ድል የሆኑበት | 1887 | 93 |
| 5 | የአድዋ ድል የተገኘበት | 1888 | 92 |
| 6 | ንጉሥ ተክለሃይማኖት ያረፉበት | 1893 | 87 |
| 7 | ልዑል ራስ መኮንን ያረፉበት | 1898 | 82 |
| 8 | አጼ ምኒልክ ያረፉበት /ልጅ እያሱ የነገሡበት/ | 1906 | 74 |
| 9 | ራስ ሚካኤል በወሎ፣ በትግራይና በጐጃም የነገሡበት | 1907 | 73 |
| 10 | ንግሥት ዘውዲቱ የነገሡበት ቀዳማዊ ኀይለሥላሴ አልጋወራሽ የሆኑበት | 1909 | 71 |
| 11 | የሠገሌ ጦርነት የተካሄደበት | 1909 | 71 |
| 12 | አቴጌ ጣይቱ ያረፉበት | 1910 | 70 |
| 13 | የህዳር በሽታ የነበረበት | 1911 | 69 |
| 14 | ልጅ እያሱ የተያዙበት | 1913 | 67 |
| 15 | የባርያ ነፃነት ደንብ የወጣበት | 1916 | 64 |
| 16 | ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ያረፉበት | 1918 | 62 |
| 17 | አቡነ ማቴዎስ ያረፉበት | 1919 | 61 |
| 18 | ንግሥት ዘውዲቱ ያረፉበት | 1922 | 58 |
| 19 | ራስ ጉግሣ ወሌ በጐንደር የሞቱበት | 1922 | 58 |
| 20 | ቀዳማዊ ኀይለሥላሴ የነገሡበት | 1923 | 57 |
| 21 | የወልወል ግጭት የተደረገበት | 1927 | 53 |
| 22 | የማይጨው ጦርነት የተካሄደበት ኢጣልያ ወደ ኢትዮጵያ የገባችበት | 1928 | 52 |

## ትግራይ

| ወረዳ | ከተማ |
|---|---|
| ዓድዋ | |
| አዲአርበአታ | ራማ |
| አገስ | ገረሁሥርናይ |
| በዛት | በዛት |
| አንቅጪ | አንቅጪ |
| አድዋ ከ | አድዋ |
| ሐሐያሌ | ፈረስማይ |
| አምበሠ ነይቴ | ነባስት |
| አህሣአ | መርሐህናይ |
| አንደበ ዓህማ | ዕዳጋ ዓርቢ |
| አንዓፈስቢ | ማይቅነጣል |
| ዓጋሜ | |
| ጐሎመኪዳ | ዘሉአንበሳ |
| ዓሉል | ዓሉል |
| ስቡሀና በአለአ | ዕዳጋሐሙስ |
| ሁለት በለሳ | ሀውዜን |
| ጋንታአፈሹም | አዲግራት |
| ሁለት አውላሎ | |
| ዓዕብ አምባ | ሠንቃጣ |
| አዱቢ | እንዳሥላሴ |
| በራህሌ | በራህሌ |
| ፅራዕ | አጉላዕ |
| እንደርታ | |
| ገረአልታ | ጭኄረዳ |
| እንደርታ | መቀሌ |
| ዱዱበና ደርጋአጀን | ኲሐ |
| ሻከት | ሻከት |
| ጎጅራት | ደቡብ |

| ወረዳ | ከተማ |
|---|---|
| እንደርታ | |
| አፍደራ | አፍደራ |
| ሕንጣሎ | ሕንጣሎ |
| ሠሐርቲ | ግጀት |
| ሰሉዋ | ደሰ |
| ዋዕረብ | ሣምሬ |
| ራያና አዘቦ | |
| መሆኒ | መርባ |
| አምባላጌ | አደሸሁ |
| ዲዲግሣአሳ | ዲዲግሣአሳ |
| ጨርጨር | ወይራውሃ |
| በራ | ቻለና /ሸበና |
| እንዳመሆኒ | ማይጨው |
| ተምቤን | |
| ዐፀራት | ወርቅ አምባ |
| ደጋ ተምቤን | ሀገረሰላም |
| አምበረመጢቃ | ጉያ |
| ጣንቋምሳሽ | አግቤ |
| አበርገሌ | ነየየ |
| አክሱም | |
| ማራይ | ውቅሮ |
| ሰይማይጨው | [illegible] |
| ታችማይጨው | አዲቀርኒ |
| አዴት | ደብረ ገነት |
| ናአዴር | ማህበረ ፅጋ |
| ዘና | ደብረ ከርቢ |

ትግራይ /የቀጠለ/

| ወረዳ | ከተማ |
|---|---|
| **ሽሬ** | |
| ታችአድያቦ | ሽርጋ |
| ለዒላይ አድያቦ | አዲአዘወዳለ |
| ላይ አዲያቦ | ኢዲዳበር |
| መደባይታበር | ሰመማ |

| ወረዳ | ከተማ |
|---|---|
| **ሽሬ** | |
| ታች ቆራሮ | እንዳስላሴ |
| ሐደጉቶ | ሺራሮ |
| አስገዴ | ማይተሰማያ |
| ፅምበላ | እንዳባጉና |
| ጉልትወዳጁ | ሰላከላካ |

---

**ወሎ**

| ወረዳ | ከተማ |
|---|---|
| **ራያና ቆቦ** | |
| አላማጣ | አላማጣ<br>ዋጃ |
| ቆቦ | ቆቦ<br>ሮቢት<br>ጉብጎ |
| **የጁ** | |
| ጉባላፍቶ | ወልድያ |
| ሀብሩ | መርሳ<br>ወርጌሳ<br>ሲርንቃ |
| **አምባሰል** | |
| አምባሰል | ውጫሌ |
| ተሁለደሬ | ሐይቅ<br>ቡሉስ<br>ቦሩ ደብረብርሃን<br>ጋሰሚሌ |
| ወረባቦ | ቦከከሳ<br>ቢስቲማ |
| **ቃሉ** | |
| ባቲ | ባቲ |
| ቃሉ | ሐርቢ<br>ኮምቦልቻ |
| ደወይራሕመዶ | ቦራ |
| አርጡማ | ጨፋ |

| ወረዳ | ከተማ |
|---|---|
| **ቃሉ** | |
| አባጉ ጉሳ | ከሚሴ |
| አላቡኩ | ደጋጋ |
| **ደሴ ዙሪያ** | |
| ኩታ በር | ኩታበር |
| ደሴ ዙሪያ | ደሴ |
| **ወረኢሉ** | |
| ወረኢሉ | ወረኢሉ<br>ከቤ |
| ጃማ | ደጉሉ |
| ለገሂዳ | ወይን አምባ<br>ለገሂዳ |
| **ቦረና** | |
| ባይንት | አገባር |
| ደብረሲና | መካነሰላም<br>ወገዲ<br>ቦቆ |
| ከላላ | ከላላ |
| **ወረሂመኖ** | |
| ተንታ | አጅባር<br>ተንታ |
| ለጋምቦ | አቀስታ |
| መቅደላ | መቅደላ |